# የኢታኖል ቤንዚን ድብልቅ ነዳጅ ጥቅም ላይ ለማዋል የወጣ መመሪያ

አዲስ አበባ
መጋቢት 1992

መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## መግቢያ

ከከርሰ ምድር የሚወጣው ነዳጅ ዘይት አላቂ ከመሆኑም በላይ በአብዛኛው ለትራንስፖርትና ኢንዱስትሪ አገልግሎት ሲውል የአካባቢ ብክለት የሚያስከትል በመሆኑ የነዳጅ ዘይት ሀብት ያላቸውና የበለፀጉ ሀገሮች ለታዳሽ ኢነርጂ ምንጮች ልማትና አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት እየሰጡ ናቸው::

ሀገራችን ኢትዮጵያም በግንቦት 1986 ዓ.ም. ባወጣችው የኢነርጂ ፖሊሲ ላይ ለትራንስፖርት አገልግሎት የሚውለው የነዳጅ ዘይት በከፊልም ቢሆን ለመተካት የሚያስችል የሀገር ውስጥ ምርት ጥቅም ላይ እንዲውል መንግሥት አስፈላጊውን ትኩረት እንደሚሰጥ ተመልክቷል:: የአካባቢ ጥበቃና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲዎችም ይህንኑ የትኩረት አቅጣጫ በበለጠ የሚያጠናክሩ ናቸው::

በተለያዩ ሀገሮች ጥቅም ላይ ከዋሉት ታዳሽ የኢነርጂ ምንጮች መካከል ሞላሰስ ከሚባለው የስኳር ተረፈ ምርት ወይም ከተብላላ ስታርች የሚመረተው ኢታኖል የተሰኘው የአልኮል ዓይነት አንዱ ሲሆን በሀገራችንም የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ይህን ኢታኖል ማምረት ጀምሯል::

በሀገር ውስጥ የተመረተውን ኢታኖል ከቤንዚን ጋር ደባልቆ ለገበያ ማቅረብ:-

- የውጭ ምንዛሪ ለማዳን፣
- የአካባቢ ብክለት ከመቀነስ፣
- የሀገር ውስጥ ተረፈ-ምርት ጥቅም ላይ ከማዋል፣
- የነዳጅ ይዘትን (ኦክቴን ቁጥር) ከማሻሻልና ከተሽከርካሪዎች የሞተር ደህንነት አኳያ ጠቀሜታ ስላለው ኢታኖል ከቤንዚን ጋር ተደባልቆ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት መቀየስ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል::

በመሆኑም ይህን መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል::

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «የኢታኖል-ቤንዚን ድብልቅ ምርት፣ ስርጭትና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 276/203 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በቅድሚያ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በቤንዚን ተጠቃሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል:: ለወደፊት የኢታኖል ምርት እየጨመረ ሲሄድ በክልሎች ተፈፃሚ የሚሆንበት ሁኔታ በመንግሥት ይመቻቻል::

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## 3. መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት

3.1 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

3.2 የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን

3.3 የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ

3.4 ነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች

3.5 የነዳጅ ማደያዎች

## 4. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣

4.1 የኢታኖል-ቤንዚን ድብልቅ ታሪፍ አጥንቶ እያዘጋጀ ለመንግሥት ውሣኔ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ለህብረተሰቡ በማሳወቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል::

4.2 የኢታኖል ምርት መጠን ማደጉ ከፊንጫ ስኳር ፋብሪካ መረጃ ሲደርሰው የኢታኖል ቤንዚን ድብልቅን ከመቶ ድርሻ (ፐርሰንታይል) ሊያሻሽል ይችላል:: ሆኖም በድብልቁ ውስጥ የኢታኖል ከመቶ ድርሻ (ፐርሰንታይል) ከአስር በመቶ (10%) መብለጥ የለበትም::

4.3 የኢታኖልና የኢታኖል ቤንዚን ድብልቅ ምርት፣ ክምችትና ስርጭት መረጃዎችን ከፊንጫ ስኳር ፋብሪካና ከነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች ያሰባስባል::

4.4 የኢታኖል ቤንዚን ድብልቅ ስርጭት የሚቋረጥበት ሁኔታ የሚከሰት መሆኑን ሲያውቅ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለመንግሥት ሃሣብ ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊነቱን ይከታተላል::

## 5. የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን የኢታኖል፣ የቤንዚን እና የኢታኖል-ቤንዚን ድብልቅ ጥራትና ደረጃ በማዘጋጀት ለመንግሥት አቅርቦ ያስወስናል::

## 6. የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ተግባርና ኃላፊነት

የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ፣

6.1 ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ ኢታኖል እያመረተ ለነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች ያቀርባል::

መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

6.2 ለ3 ወር የሚበቃ የኢታኖል ክምችት ይይዛል፡፡

6.3 ምርት የሚቋረጥበት ሁኔታ ሲያጋጥም ወዲያውኑ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

6.4 ምርት፣ ክምችትና ስርጭትን የሚመለከቱ መረጃዎች ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና ለማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር በየጊዜው ያቀርባል፡፡

7. <u>የነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

የነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች፣

7.1 የሚቀርብላቸውን ኢታኖል ደረጃና ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን አረጋግጠው በመረከብ በይዘት መጠን ስድስት በመቶ (6%) ኢታኖል ከዘጠና አራት በመቶ (94%) ቤንዚን ጋር በማደባለቅ የኢታኖል ቤንዚን ድብልቅ አዘጋጅተው ለነዳጅ ማደያዎች ያከፋፍላሉ፡፡

7.2 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢታኖል ቤንዚን ድብልቅ መጠንን አስመልክቶ በየወቅቱ የሚያወጣውን ማሻሻያ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

8. <u>የነዳጅ ማደያዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

የነዳጅ ማደያዎች፣

8.1 ከነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች የሚቀርብላቸውን የኢታኖል-ቤንዚን ድብልቅ ሬጣን የጥራት ፍተሻ በማድረግ ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን አረጋግጠው ይረከባሉ፡፡

8.2 የኢታኖል ቤንዚን ድብልቅ መንግሥት በሚያወጣው የችርቻሮ ታሪፍ መሠረት ለቤንዚን ተጠቃሚዎች ይሸጣሉ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

# Council of Ministers Directive on the Production, Distribution and Control of Ethanol-Gasoline Blended Fuel

Addis Ababa
April, 2000

RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

7. <u>Duties and Responsibility of Fincha Sugar Factory</u>

Fincha Sugar Factory shall:

7.1 produce and supply ethanol of accepted quality and standard to the oil distribution companies.

7.2 keep ethanol stock that will be sufficient for three months.

7.3 immediately notify appropriate Authorities if it anticipates interruption of ethanol production.

7.4 submit data periodically to Ministry of Trade and Industry and Ministry of Mines and Energy regarding the production, stock and distribution of ethanol.

8. <u>Duties and Responsibilities of Oil Distribution Companies</u>

Oil Distribution Companies shall:

8.1 receive ethanol after approving its quality and standards prepare ethanol gasoline blended fuel with the mix ratio of 6% ethanol with 94% gasoline and distribute the same to filling station.

8.2 apply changes of ethanol-gasoline mix ratio periodically given by the Ministry of Trade and Industry.

9. <u>Duties and Responsibilities of Filling Stations</u>

Filling Stations shall:

9.1 receive ethanol-gasoline blended fuel from Oil Companies by approving its quality with quick quality test.

9.2 sell ethanol-gasoline blended fuel to gasoline consumers in according with the retail tariff set by the Government.

RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

3. **Permission**

The sale of Ethanol-Gasoline Blended Fuel is hereby permitted by the Government.

4. **Responsible Authorities**

4.1 Ministry of Trade and Industry
4.2 The Quality and Standards Authority of Ethiopia (QSAE)
4.3 Fincha Sugar Factory
4.4 Oil Distribution Companies
4.5 Filling Stations

5. **Duties and Responsibilities of Ministry of Trade and Industry**

Ministry of Trade and Industry shall:

5.1 study, prepare, and submit ethanol-gasoline blend fuel tariff to the Government; and announce to the public and follow up its implementation upon approval.

5.2 change ethanol-gasoline mix ratio upon receipt of the information from Fincha Sugar Factory regarding the increase of ethanol production. However, the mix ratio of ethanol in the blend may not exceed ten percent (10%).

5.3 gather information from Fincha sugar factor and Oil Companies regarding the stock and distribution of ethanol-gasoline blended fuel.

5.4 take appropriate measure when it realizes that there are circumstances which interrupt ethanol-gasoline blend supply.

6. **Duties and Responsibility of Quality and Standards Authority of Ethiopia**

The Quality and Standards Authority of Ethiopia shall prepare and submit to the government the quality and standards of ethanol, gasoline and ethanol-gasoline blended fuel for approval.

RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum